G. Meskel Azebete FSC

FHC

የወ/መ/ቁ.6463

መጋቢት 15 ቀን 1995ዓ.ም

ዳኞች፣- ተገኔ ጌታነህ

ደስታ ገብሩ

አሰግድ ጋሻው

ይ/ባይ፣- ልዩ ዐ/ሕግ ዘበነ ሐጐስ - ቀረበ

መ/ሰጪዎች፣- 1. ብ/ጄ ገብረመስቀል አዝብጤ ከጠበቃ አለሙ ደነቀው ጋር ቀረቡ

2. አቶ ተስፋዬ መኮንን -በሌሉበት

3. ኮ/ል ቁምላቸው ደጀኔ - በሌሉበት

4. ሻምበል ጌታቸው ፍስሀ - ቀረቡ

5. ብ/ጄኔራል ግርማ አየለ ከተከላካይ ጠበቃ ሽመልስ በየነ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

ይግባኙ የቀረበው የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.944/89 በ9/5/93ዓ.ም በሰጠው ብይን ላይ ቅር በመሰኘት ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጪዎች በሥር ፍ/ቤት ቀርቦባቸው የነበረው ክስ የወ/መ/ህ/ቁ. 32/1/ለ/እና 281/ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ በጊዚያዊ ወ/መንግሥት በነበራቸው ሥልጣን በአንድነት ሲሰሩ በዚህ ክስ ውስጥ ስማቸው ካልተጠቀሰው ከሌሎች ግብረ አበሮቻቸው ጋር በፖለቲካ ተሳስሮ የተቋቋመውን የሕብረብሔር ማህበራዊ የሆነ አንድ ክፍል ህዝብ በመላው ወይም በከፊል ለማጥፋት በግብረአበርነት በማቀድ የጥፋቱን ሥራ በማቋቋም ትዕዛዝ በመስጠት እንዲሁም ይህንን አድርጉት ሥራ ላይ በማዋል የኢ.ሕ.አ.ፓ.፣ የኢ.ዲ.ዩ. የኤርትራ ገንጣይ ቡድኖች አባላት በማለት ለህግ ተቃራኒ በሆነ መንገድ በክሱ ላይ ስማቸው የተጠቀሱትን እነ ሌ/ኩ/በለጠ ተፈራ፣ 66 ሰዎችን ህዳር 9/1970ዓ.ም ሌሊት ከአስመራ ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኘው ትራክስ በተባለ ቦታ ላይ ባልታወቀ መሣሪያ እንዲገደሉ በማድረግ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ሲሆን፣ ይህንኑ ክስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.113 መሠረት በአማራጭም የወ/መ/ህ/ቁ.522 ተጠቅሶ ክስ የቀረበባቸው ናቸው፡፡

ተከሳሾች ክሱን ክደው በመከራከራቸውም የልዩ ዐቃቤ ሕግ አምስት ምስክሮች በችሎት አቅርቦ በማሰማት፣ ሁለት ምስክሮች ደግሞ በምርመራ ወቅት ሰጡት የተባለውን

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን 02/03/96

የምስክርነት ቃል እና የሰነድ ማስረጃም በማቅረብ ካስረዳ በኋላ በመጨረሻ ፍ/ቤቱ ክሱንና ማስረጃውን መርምሮ የልዩ ዐ/ሕግ ማስረጃ ተከሳሾች በክሱ የተጠቀሰባቸውን ድርጊት መፈጸማቸውን ከምክንያታዊ ጥርጣሬ ውጪ አያስረዳም በማለት ተከሳሾች መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነፃ እንዲሰናበቱ በድምፅ ብልጫ ብይን የሰጠበት መሆኑን የሥር መዝገቡ ያስረዳል፡፡

ይግባኙም የቀረበው በዚህ ብይን ላይ ይ/ባይ በ17/8/93ዓ.ም ፅፎ ያቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ማመልከቻም የወንጀሉ አፈጻጸም 4ኛ ተከሣሽ በወቅቱ በጦሩ ውስጥ የነበረውን የፖለቲካ ሥልጣን በመጠቀም ከሟቾች አንዱ የሆነውን ም/መ/አለቃ ምሩፅ ኪዳነማርያምን በእረፍት ላይ ከነበረበት የጦር ካምፕ እንዲወሰድ ካደረገ በኋላ በተያዘበት ሌሊት ከሌሎች 65 ሰዎች ጋር እንዲገደሉ በማድረግ ከ3ኛ ተከሳሽ ጋር በግድያው ቦታ ላይ በመገኘት ግድያውን ሲያስፈጽሙ፣ 1ኛ፣ 2ኛ፣ 5ኛ፣ ተከሣሾች ደግሞ 66ቱ ሰዎች እንዲገደሉ በስብሰባ ተስማምተው ፈርመዋል፡፡ ለዚህም ዐ/ሕግ የሰውና የፅሁፍ ማስረጃ አቅርቦ በሚገባ አስረድቷል፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤቱ ከአምስቱ ሦስቱ ምስክሮች የሰጡት ቃል በተራራቀና ባልተመሳሰለ ሁኔታ የተሰጠ ነው በማለት ቃላቸውን ውድቅ ማድረጉ አግባብ አይደለም፡፡ ወንጀሉ የተፈጸመው ከ23 ዓመት በፊት እንደመሆኑ በውሣኔው በድምፅ የተለዩት ዳኛ እንደገለጹት ከጊዜው ርቀት አንፃር ምስክሮች ሁኔታውን በአንድ ዓይነት አገላለፅ ይገልፃሉ ተብሎ የሚገመት አይደለም፡፡ ምስክሮቹ የተለያዩት በድርጊት አንድ ክፍል ማለትም ከሟቾች አንዱ የሆነው ምሩፅ ኪ/ማርያም ከቤቱ አካባቢ በተከሳሽ አማካይነት መወሰዱን በሚመለከተው ነጥብ ላይ ብቻ ሲሆን ሌላው የድርጊቱ ክፍል የሟች ምሩፅ ኪ/ማርያም እና የሌሎች 65 ሰዎች አገዳደል በሚመለከት በችሎት የመሰከረው 4ኛ ምስክር እንደመሆኑ ሌሎች ግን በዚህ ጊዜ በቦታው ስላልነበሩና ቃላቸውንም በዚህ ነጥብ ላይ ስላልሰጡ የምስክርነት ቃላቸው ሊጋጭ የሚችልበት ሁኔታ ስለሌለ፣-

የዚህ ምስክር ቃልም በምርመራ ወቅት የተሰጠ ቃሉን ካያያዝነው የምስክር ቃል ተመሣሣይነት ያለውና የሚደጋገፍ በመሆኑ የሟች ምሩፅ ኪ/ማርያም አያያዙ ግልፅ አይደለም ቢባል እንኳ 66ቱ ሰዎች መገደላቸውን በሚመለከት የቀረበው ማስረጃ በግልፅ አንዱ ካንዱ ጋር በተደጋገፈ ሁኔታ የቀረበ በመሆኑ እንዲሁ በሌላ ጭብጥ ላይ የተነሳውን ልዩነት ምክንያት በማድረግ የሰዎቹ መገደል አልተረጋገጠም ሊባል አይችልም፡፡ የውሣኔው አሰጣጥ የወንጀል ድርጊት የተፈጸመበት የጊዜና የአካባቢ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል ፡፡ በዚህ መልኩ ሳይታይ ቀርቶ ልዩነቶችን ብቻ በቁንፅል ወስዶ ጠቅላላው የክሱና የማስረጃው ውህደት መፍረስ አይገባውም፡፡

የፅሁፍ ማስረጃውን በሚመለከትም የተከሣሾች ፊርማ በየገፁ አልተቀመጠም፤ በሰነዱ ላይ ያረፈው ፊርማ የተከሣሾች ለመሆኑ በባለሙያ አልተረጋገጠም በማለት ማስረጃውን ውድቅ ማድረጉ አግባብ አይደለም ሲል በዝርዝር ጠቅሶ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
02/03/96

የሰነዱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ተጨማሪ ማስረጃዎችን አስቀርቦ እንዲመለከትና ቅሬታውን በዝርዝር ተቀብሎ የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር መ/ሰጪዎች እንዲከላከሉ ትዕዛዝ እንዲሰጥበት በማለት ጠይቋል።

የቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ ማመልከቻም ለማጣራት መ/ሰጪዎች ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት የተደረገ ሲሆን፣ 2ኛና 3ኛ መ/ሰጪዎች ጥሪ ተደርጉላቸው ባለመቅረባቸው በሌሉበት ጉዳያቸው እንዲታይ ትዕዛዝ ተሰጥቶበታል። ሌሎች መልስ ሰጪዎች ቀርበው 1ኛ እና 4ኛ መ/ሰጪዎች በ17/4/94ዓ.ም በየራሳቸው የጻፉትን 5ኛው መ/ሰጪም ሐምሌ 25/94ዓ.ም የተጻፈ መልስ በዝርዝር አቅርበው በዐ/ሕግ በኩል የቀረቡት ምስክሮችም ሆኑ የፅሁፍ ሰነዶች አንዳቸውም እንደክሱ ለመፈጸማችን ከምክንያታዊ ጥርጣሬ ውጪ አላረጋገጡብንም። በዚህም ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማፅናት እንዲያሰናብተን ሲሉ ያመለከቱበት ነው።

ይ/ባይም በመጨረሻ የመ/መልሱን በ23/01/95ዓ.ም በተጻፈ አቅርቦ እንደ ይግባኝ ቅሬታው ታይቶ እንዲወሰንለት ጠይቋል።

እኛም በቀረበው የይግባኝ ክርክር መነሻነት ዐ/ሕግ በሥር ያቀረባቸው የሰውና የፅሁፍ ማስረጃዎች እንደክሱ አስረድተዋል ወይስ አላስረዱም? መ/ሰጪዎችስ በሥር ሳይከላከሉ በነፃ የተሰናበቱት አግባብ ነው? አግባብ አይደለም? የሚሉትን ነጥቦች የሥር መዝገቡን በማስቀረብ አንድ በአንድ በማየትና ከህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናቸዋል።

የልዩ ዐቃቤ ሕግ በሥር በአሁኑ መ/ሰጪዎች ላይ አቅርቦት የነበረው ክስ ከላይ እንደተገለፀው የወ/መ/ሕ/ቁ.32/1/ለ/ እና 281/ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ ስማቸው በክሱ ላይ የተዘረዘሩት 66 ሰዎች የኢህአፓ፣ የኢዲዩ፣ የኤርትራ ገንጣይ ቡድኖች፣ አባላት በማለት ለህግ ተቃራኒ በሆነ መንገድ ህዳር 9/70ዓ.ም ሌሊት ከአስመራ ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኝ ትራክስ በተባለ ቦታ ባልታወቀ መሣሪያ እንዲገደሉ አድርገዋል የሚል ነው።

ለዚህም ዐቃቤ ሕግ አምስት ምስክሮችን በችሎት አስቀርቦ ማስማቱን፣ ሁለት ምስክሮች ደግሞ በምርመራ ወቅት የሰጡትን ቃል እና 66ቱ ሰዎች አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ውሣኔ ተሰጠበት የተባለውን የሠነድ ማስረጃ ጭምር ማቅረቡን የሥር መዝገቡ ያስረዳል።

ይህም በመሆኑ እነዚህኑ በሥር የቀረቡትን የልዩ ዐ/ሕግ የሰውና የፅሁፍ ማስረጃ ተመልክተናቸዋል። በሥር ውሣኔው ላይ እንደሠፈረውም ከሁለት እስከ አራት የተጠቀሱት የልዩ ዐ/ሕግ ምስክሮች ቀርበው ም/መ/አለቃ ምሩፅ ኪ/ማርያም እንዴት እንደተያዘና ስለአገዳደሉም ያስረዱ ናቸው። ሦስቱም ምስክሮች መ/አለቃ ምሩፅ ተጠርቶ ሲወሰድ እቦታው ነበርን ያሉ ናቸው። ነገር ግን 3ኛዋ ምስክር ባለቤታቸው 4ኛዋ ምስክር እንደሆኑ ጠቅሰው በወቅቱ መ/አ ምሩፅ ሲወሰድ ባለቤቱ በረሃ ስለነበር እቦታው አልነበረም ያሉ ሲሆን



02/03/96

4ኛው ምስክር ግን በወቅቱ እዚያው እቦታው ነበርኩ አይቻለሁ ያሉ ናቸው፡፡ ይህም የምስክሮች ቃል ልዩነት ያለው መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን፣ በሥር ውሣኔው ላይም ይኸው ተጠቅሷል፡፡

በሌላ በኩልም ይኸው በችሎት ቀርቦ የመሰከረው 4ኛው የልዩ ዐ/ሕግ ምስክርና በምርመራ ወቅት የምስክርነት ቃሉን ሰጠ የተባለው መጋቢ ሃምሣ አለቃ ታምሩ ወርቄ የሰጠውን የምስክርነት ቃል እንደተመለከትነው ግድያው ሲፈጸም ሁለቱም አይተናል በቦታውም ነበርን ያሉ ናቸው፡፡

ስለግድያው አፈጻጸም በ4ኛው የልዩ ዓ/ሕግ ምስክር የተነገረው ከየሻምበሉ ጦር አስር፣ አስር፣ ወታደሮች ተመርጠው ወደ ቃኘው ትሄዳላችሁ እንደተባሉና መኪና ላይ ተጭነው እንደሄዱ፣ ከዚያም ወደ ወህኒ ቤቱ እንዲሄዱ ተደርጉ ወህኒ ቤቱ በር ላይ ቆመው እንዳሉ እስረኞች በሰንሰለት ታስረው ከወህኒ ቤቱ ወጥተው መኪና ላይ ሲጫኑ ማየቱን፣ ምሩፅንም በቁመናውና በድምፁ እንዳወቀው፣ እኔን የሚያስገዱልኝ ሻ/ል ጌታቸው ፍስሐና ሻለቃ አስመላሽ ማሩ ናቸው እያለ መ/አለቃ ምሩፅ ሲጮህ መስማቱን፣ እስረኞቹ በመኪና ተጭነው ይዘዋቸው የሄዱትም ቁሺት ወደተባለ ቦታ መሆኑን፣ በሌሎች ብዛት ያላቸው መኪና እስረኞች ተጭነው መጥተው ወደ ተቆፈረው ጉድጓድ አፋፍ ተወስደው ሲረሸኑ እንዳየ፣ እነዚህም ወደ 68 የሚሆኑ ሰዎች መሆናቸውን ይህንንም ያወቀው በካቴናው ብዛት መሆኑን ይኸውም ከ34 ካቴና አንዱ ጠፋ ሲባል መስማቱን፣ ርሸናው የተፈጸመው ህዳር 9/70 ዓ.ም ከምሽቱ 4 ሰዓት እስከ 5 ሰዓት እንደሆነ፣ የግድያውን ትዕዛዝም የሰጡት ኩ/ል ቁምላቸው መሆኑን፣ ሌሎች የጦር አዛዦችም እንደተገኙ ሻ/ል ጌታቸውም እዚያው እንደነበር፤ ከተረሸኑት ሰዎች መሐልም የሚያስታውሰው ሌ/ኮ/ል በለጠ ተፈራ፣ ም/መ/አለቃ ምሩፅ ኪ/ማርያም፣ አስር አለቃ ገ/ፃዲቅ ካሣዬ ም/አ/አለቃ ክብረመንግሥት ገብሩ፣ ዳይኑ ሐጐስ የተባሉትን እንደሚያውቅ ምስክሩ ማስረዳቱን የሥር መዝገቡ ያስረዳል፡፡

መጋቢ ሃምሣ አለቃ ታምሩ ወርቄ በምርመራ ወቅት ሰጠ ተብሎ በቀረበው የምስክርነት ቃል ደግሞ የተነገረው መ/አለቃ ምሩፅ ቆስሎ ሆስፒታል ሲታከም መቆየቱን፣ ከሆስፒታል ወጥቶ አንድ ቀን ቤቱ እንዳደረ ህዳር 9/70ዓ.ም ሻ/ል ጌታቸው ፍስሀ ከቃኘው ሻለቃ መትረየስ የተጠመደ ጂፕ መኪና ልኮ በማስወሰድ አንድ ቀን እስር ቤት ካሳደረው በኋላ በማግስቱ ህዳር 10/70ዓ.ም ቀን በግምት 9 ሰዓት አካባቢ ወደ አስመራ ከተማ ወጣ ብሎ ትራክስ ከሚባል ቦታ ከሌሎች አራት በሌላ ማዕረግ አባሎች ጋር እንደረሸናቸው፣ ከተረሸኑት ውስጥ ም/መ/አለቃ ክብረመንግሥት ገብሩም የጓድ መሪ የነበረውም እንደሚገኝበት ከጦሩ መካከል ተመልካች መሄድ ስላለበት እኔም በዕለቱ ተመልካች ስለነበርኩ በቦታው ተገኝቼ ሻ/ል ጌታቸው መፈክር እያሰማ ቆሞ በገዳዮች

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን 02/03/96

ሲያስገድል አይቻለሁ፡፡ ትዕዛዝ በመስጠት በጥይት ተደብድበው እንዲገደሉ ያደረገው ሻ/ል ጌታቸው ነው በማለት ምስክሩ ሰጠ የተባለው ቃል ያስረዳል፡፡

ከዚህ የምንረዳውም 4ኛው የልዩ 0/ሕግ ምስክር ም/መ/አለቃ ምሩፅን ጨምሮ 68 ሰዎች ከአስመራ ወጣ ብሎ ቁሺት ወደተባለ ቦታ ተወስደው ህዳር 9/70ዓ.ም ከምሽቱ ከ4-5 ሰዓት ባለው ጊዜ ሲረሸኑ አይቻለሁ፣ እንዲረሸኑ ትዕዛዝ የሰጠውም ኰ/ል ቁምላቸው ነው ያለ ሲሆን የምስክርነት ቃሉ ሰጠ የተባለው መጋቢ ሃምሣ አለቃ ታምሩ ወርቄ ደግሞ ም/መ/አለቃ ምሩፅ ህዳር 10/70ዓ.ም በግምት ከቀኑ 9 ሰዓት አካባቢ ወደ አሥመራ ከተማ ወጣ ብሎ ትራክስ ከሚባል ቦታ ከሌሎች 4 ባለሌላ ማዕረግ አባሎች ጋር ተወስደው ሻ/ል ጌታቸው ፍስሀ መፈክር እያሰማ ቆሞ ትዕዛዝ በመስጠት ሲያስረሽን እቦታው ተገኝቼ ተመልክቻለሁ፣ ያለ ነው፡፡

ይህም የልዩ 0/ሕግ አንድን ጉዳይ ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች የተራራቁ፣ ርስበርሳቸው የተጋጩ ፣ በተቃራኒ መልኩ የሚያስረዱ መሆኑን ስለሚያሳዩ የምስክሮች ቃል በርግጥም አጠራጣሪና እምነት የሚጣልበት እንዳልሆነ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የፅሁፍ ማስረጃውን በተመለከተም በመጀመሪያው ገፅ ላይ የለየላቸው የኢሕአፓ፣ የኢዲዩ፣ የኤርትራ ተገንጣይ ቡድኖች አባላት የሆኑ ስማቸው የተዘረዘሩት ፀረ አብዮተኞች ላይ አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው በማለት የተወሰነ መሆኑን ተጠቅሶ ውሣኔው የተሰጠበት ቀንም በዚያው ገፅ ግርጌ ተገልጿል፡፡ በዚሁ ገፅ ላይም ግልባጭ የተደረገላቸውን አካላት ጭምር አሳይቷል፡፡ ነገር ግን በዚህ በዋናው ውሣኔ ላይ ውሣኔ ሰጡ በተባሉት በአንዱም አልተፈረመበትም የአሁን 1ኛ፣ 2ኛ እና 5ኛው መ/ሰጪዎች ፈረሙ የተባሉትም ከዚሁ የፅሁፍ ማስረጃ ጋር የተያያዘ ከ2ኛው ገፅ ጀምሮ የ66 ሰዎች ስም ዝርዝር ተጠቅሶ በመጨረሻው በ4ኛው ገፅ ላይ ብቻ ስምና ፊርማ መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ስምና ፊርማ በርግጥ በገፅ 1 ላይ የተጠቀሰውን ውሣኔ የሰጡ ናቸው የሚለውን በተጨባጭ የሚያስረዳ መሆኑን አያመለክትም፡፡ በውሣኔው ላይ እርምጃው የሚወሰድባቸውን ስማቸው ከተዘረዘሩት ውስጥ በአንዱ በእነ እገሌ ላይ ተብሎ እንኳን ባለመጠቀሱ ውሣኔው በስተመጨረሻ በፈረሙት ሰዎች የተሰጠ ነው ብሎ ለማያያዝ እንዳይቻል ሌላ ደጋፊ ማስረጃም ስለሌለው ሠነዱን በእጅጉ አጠራጣሪ እንዳደረገው ተገንዝበናል፡፡

ከዚህም ባሻገር በሰነዱ ላይ ፈረሙ በማለት በተባሉት በመ/ሰጪዎች የተፈረመ መሆን አለመሆኑ በቴክኒክ ምርመራ ተጣርቶ እንዲረጋገጥ የልዩ 0/ሕግ በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲታይለት ጠይቋል፡፡ ነገር ግን ከላይ በተመለከተው መሠረት በስተመጨረሻው ያለው ስምና ፊርማ በሰነዱ የመጀመሪያው ገፅ ላይ የተጠቀሰውን ውሣኔ የሰጡ ለመሆኑ ማስረጃው ራሱ አጠራጣሪ እንዳደረገው ተመልክተናል፡፡ ይህ እስከሆነ ድረስ ደግሞ የፊርማው መጣራት አለመጣራት ጠቀሜታ የሚኖረው ስለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን አቤቱታም የምንቀበለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ የልዩ 0/ሕግ ያቀረባቸው የሰውና የፅሁፍ ማስረጃዎች እንደክሱ ያላስረዱ፣ ርስበርሳቸው የተቃረኑና ያልተመሣሰሉ በመሆናቸው በመ/ሰጪዎች ላይ ተጠቅሶ የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነፃ እንዲሰናበቱ የሥር ፍ/ቤቱ በአብልጫ ድምፅ የሰጠው ብይን ተገቢ ነው ብለን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.195/1/ መሠረት በማፅናት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡ ቁጥር 944/89 የሆነውም የሥር መዝገብ ይመለስ ብለናል፡፡

የዳኞች ፊርማ፣- ተገኔ ጌታነህ

ደስታ ገብሩ

አሰግድ ጋሻው

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት 02/03/96

/አ.ገ